# መድረክና «ሰማዕታቱ»

ተወልደብርሃን ክፍሌ (tewoldek@yahoo.com)

ለዚህ ርዕስ መነሻ የሆነኝ በጥቅምት አጋማሽ አከባቢ የመድረክ አመራሮቹ ገብሩ አስራት፤ተመስገን ዘውዴ፤ ስዬ አብርሃና መረራ ጉዲና በእንግድነት ከተሰየሙበት የዋሽንግተኑ ስብሰባ ከተነሱት ነጥቦች ላይ በመመስረት ጥቂት ማለት አስፈላጊ መስሎ ስለታየኝ ነው:: ስየን በሚመለከት ከዚህ በፊት አስተያየት የሰጠሁበት ስለሆነ (http://aigaforum.com/articles/Yemeta_bimeta_siye.pdf) የዛሬ ፅሑፌ ቀሪዎቹ ሶስት ሰዎች በሰነዘሩት ሐሳብ ላይ የተመሰረተ ይሆናል::

የስብሰባው ድባብ (2 ሰዓት ከ33 ደቂቃ ጊዜየን ከፍየበታለሁ) አሸናፊዎችና ተሸናፊዎች፤ፖለቲከኞችና «ኢኮኖሚስቶች» እንዲሁም «ሰማዕታት» የተገኙበት፤ «ሞት ለህወሓትና ለወያነ» የተዜመበት እንዲሁም ደግሞ የጥቂቶች የማይባል የእናት ሀገር «ፍቅር» ሞልቶ የፈሰሰበት ይመስላል:: በእናት ሀገር ፍቅር «የነደደ» ሰው ንግግሩ ሰላማዊ ይሁን የስድብ ናዳ ጭብጨባ ያስገኝለታል:: አጨብጫቢዎቹ ምን እንደሚደግፉና እንደሚቃወሙ መለየት እስኪቸግር ድረስ ብቻ እንዲሁ ያጨበጭባሉ:: «ስየ ገዳይ ነው» ሲባል ይጨበጨባል:: «ያለፈውን ረስተን ትኩረታችን እጅ ባልሰጡት ወያኔዎች ላይ እናድረግ » ሲባልም እንዳዚሁ:: የስብሰባው መሪ የያንዳዱ ተናጋሪ ጊዜ 2 ደቂቃ ላይ ባይገድበው ኖሮ ልንሰማ የነበረው ጉድ መገመት ይከብዳል:: ትኩረቴን የሳቡት ግን የተሳታፊዎቹ ብሶት፤ ጥላቻና ስድብ ሳይሆን ተጋባዦቹ ኢትዮጵያን በሚመለከቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሰጡዋቸውን ምላሾች ናቸው:: በኢኮኖሚው ጉዳይ ልጀምር::

ሁሌ እንደሚሆነው ኢኮኖሚውን አስመልክተው ማብራሪያ የሰጡት ተመስገን ዘውዴ ናቸው::እሳቸው ኢኮኖሚስት እንደሆኑ ቢሰማቸውም ቢያንስ ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ትንታኔዎቻቸው የተሳሳቱ እንደሆኑ **ሃብታሙ አለባቸው** የተባሉ ፀሐፊ ደጋግመው ማብራሪያ ሰጥተውበታል:: ተመስገን ዘውዴ ስብሰባው ላይ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተው ነበር:: «መንግስት ወይም ገዢው ፓርቲ ከኢኮኖሚው እጁ እንዲያስወጣ፤ ከህዝብ ዘርፎ ያቋቋማቸውን ኩባንያዎች እንዲወረሱ በተደጋጋሚ አቋማችንን ግልፅ አድርገናል:: መድረክ ስልጣን ቢይዝ ደግሞ ይህንኑ ተፈፃሚ ያደርጋል» ሲሉ እንቅጩን ነግረውናል:: ፖለቲካዊ ልዩነቶቻችንን ለጊዜው ወደ ጎን ትተን መንግስት ኢኮኖሚው ውስጥ እጁን እያስገባ ያለው ወዶ ሳይሆን የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ስለሚያስገድደው በመሆኑ ብቻ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ

አይደለም:: በመሰረተ-ልማቶቻችን ላይ ገንዘባቸውን ለማፍሰስ የሚፈልጉ በቂ የግል ባለሀብቶች ቢኖሩን ኖሮ መንግስት ከተመስገን ዘውዴና መሰል የኒዮ-ሊበራል ስርዓተ-ኢኮኖሚ አቀንቃኞች ጋር የሚያጣላው ነገር ባልኖረ ነበር:: የኢኮኖሚ ትንታኔ ከተቋዋሚነት ለማስታረቅ የሚደረገውን አጉል ሙከራ ትርፉ ልፋት ከመሆን አይዘልም:: በዚህች በምንኖርባት ፕላኔት ውስጥ ወሳኝ በሆኑ ኢኮኖሚያዊ አውታሮች ላይ የመንግስትን እጅ ሳይታከልበት ያደገ ኢኮኖሚ የለም:: የካፒታሊዝም ማማ ላይ የተቀመጡቱ ሀገሮችም ቢሆኑ ሊበራሊዝም እንደ ስርዓት የኢኮኖሚ ዕድገታቸው ውጤት እንጂ ሊበራሊዝም ኢኮኖሚውን እንዳልፈጠረ ታሪክ ምስክራችን ነው:: በመጀመሪያ የዕድገት ረድፍ የተሰለፉት ሃገራት ቅኝ ግዛትን፤የላብ አደሩ ነፃ ጉልበትንና ባርነት ላይ ተመስርተው ሃብትና ባለሀብት ማፍራታቸውን መገመት ማን ሊሳነው ይችላል? የትኛው ሀገር ነው በወሳኝ የኢኮኖሚ ምሰሶዎቹ ላይ እጁን ያላሰገባው? ስንቱ የምርምር ዘርፍ ነው በግል ባለሀብት ፋይናንስ የተደረገው ውይንም የሚደረገው? በቅርቡ እንኳን እ.ኤ.አ በ2009 ዓ/ም በትሪሊዮን የሚቆጠር ንዋይ የፋይናንስ ተቋማትን ለመደጎም የዋለው ለምንድን ነው? ችግሩ ተመስገን ዘውዴን ለማሳመን ከመቻል በላይ ነው:: ገበያ ራሱን የማስተካከል ብቃት ይጎድለዋል ብቻ ሳይሆን አሁን ዓለማችንን እያመሳት ያለው የኢኮኖሚ ውድቀት ዋነኛ መንስኤው ይኸው ከልክ ያለፈ የገበያ «ፍቅር» የወለደው እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ከሞላ ጎደል የተስማሙበት ጉዳይ ሆነዋል:: ስለዚህ የዚህ ዘመን ዋነኛው አጀንዳ መንግስት ኢኮኖሚው ውስጥ እጁን ያስገባ አያስገባ ሳይሆን በዚሁ ሂደት ሊኖር የሚችል ሚዛን አጠባበቅ ላይ ያተኮረ እንደሆነ ቢገነዘቡ መልካም ነው:: የኢትዮጵያ መንግስትም ለብዙ አስርት ዓመታት ዓለም የተስማማበትንና አፍሪካን ከድህነት አዙሪት ውስጥ የከታትን የአዲሱ ሊበራሊዝም የበላይነት በብቸኝነት ተጋፍጠዋል:: ከዚህ አንፃርም የኢህአዴግ መንግስት ሊሸለም እንደሆን አንጂ ሊወቀስ የሚችልበት ክፍተት የለም::

ሌላው አሳዘኝ ትንተናቸው በባለአደራነት ስለሚተዳደሩት ኩባንያዎች የሰጡትን መግለጫ ነው:: «ከኢትዮጵያ ህዝብ ዘርፎ ያቋቋማቸው » ሲሉ በግላጭ ዋሽተዋል:: ተሰብሳቢዎቹ ሰምተው ከጣፈጡዋቸው ንግግሮች ደግሞ አንዱ ይኸው ነበር:: ስየና ገብሩ ዕውነቱን አጥርተው የሚያውቁ ቢሆኑም ለማስተካከል ግን «ሰማዕትነታቸው» አልፈቀደላቸውም:: **የጥገኛ ፖለቲካል ኢኮኖሚ አቀንቃኞች ዋነኛ ትኩረት ማን ምን ወሰደ እንጂ ማን ምንን ፈጠረ የሚል ባለመሆኑ እነዚህን ኩባንያዎች በጠላትነት ቢፈርጁዋቸው አይፈረድባቸውም**:: እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው:: እነዚህ ተቋማት ከሃያ ሺህ ለማያንሱ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠራቸውን፣ ባለፈው የበጀት ዓመት ብቻ ከ390 ሚልዮን ብር በላይ የመንግስት ግብር ገቢ ማድረጋቸውን፣ የግሉ ዘረፍ ሊሸፍናቸው ባልቻሉ መስኮችና የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ እንደሚገኙ የኩባንያዎቹ የበላይ ሃላፊት አዜብ መስፍን ገልጸዋል:: በአቅርቦት እጥረት

እየተቸገረ ያለ ኢኮኖሚ የነዚህ ኩባንያዎች መኖር ውድድሩን በምን መልኩ ኢፍትሃዊ ሊያደረገው እንዲሚቸል ተመስገን ዘውዴ መልስ የላቸውም::

ተመስገን ዘውዴ ፓርላማ ውስጥ ይሉት እንደነበረው ሁሉ በዚሁ ስብሰባም ስለ ማክሮ-ኢኮኖሚው ስሜት በተጫነው አገላለፅ እንዲህ ብለው ነበር:: «ኢኮኖሚው ሙቀት እያመጣ ነው ስንላቸው ሙቀትን በሙቀት ነው የምናስወግደው ይሉናል::» ካሉ በኋላ መድረክ ቢመረጥ ስለሚወስዳቸው እርምጃዎች በሚከተለው መልኩ አብራርተዋል:: «ዋነኛ የኢኮኖሚው ችግር ግሽበት ነው:: ስለሆነም የመንግስት የበጀት ጉድለት በመቀነስ፣ የወለድ ምጣኔ በመጨመር፣ የባንኮች ተቀማጭ (ሪዘርቭ) ከፍ እንዲል በማድረግ ወ.ዘ.ተ እንቆጣጠረዋለን:: ልማት ማለት ህንፃና መንገድ መገንባ ማለት አይደለም:: የኢትዮጵያ ህዝብ መኖር አቅቶታል::» አክለውም« እኔ የኢኮኖሚክስ እውቀት አለኝ ማለቴ ሳይሆን መንግስት ግን በእርግጠኝነት ግንዛቤው የለውም» ሲሉ እሳቸው «አዋቂ» ባይሆኑም ከመንግስት ግን « እንደሚሻሉ» ራሳቸውን ለትዝብት እስኪዳርጉ ድረስ ተመፃድቀዋል:: እኔም እንዲህ እሉታለሁ:: የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች( እንዲያውም ሁሉም ፖሊሲዎች) በመልካም አጋጣሚና በተግዳሮቶች መካከል በሚኖር ምርጫ የሚከወኑ ናቸው:: ኢኮኖሚው ሲሞቅ ማቀዝቀዝ ቀላሉ መንገድ ነው:: ግን ከፊት ለፊቱ ከረዥም ጊዜ አንፃር ፈተና የሚሆኑ አማራጮች አብረዉት አሉ:: ኢኮኖሚው ማቀዝቀዝ የሚቻለው ኢንቨስተመንትን በመቀነስ ነው:: የዚሁ ቀጥተኛ ውጤትም ዕድገት መቀነስና የስራ አጥን ቁጥር መጨመር ሲሆን ጉዳዩ ደግሞ እያሽቆለቆለ ባለ ኢኮኖሚ ላይ ሲከሰት እጅግ አደገኛ ያደረገዋል:: ኢንቨስትመንቱን እንዲቀንስ እየተፈለገ ያለው ደግሞ መንግስት በመሆኑና በወሳኝ ኢኮኖሚያዊ አውታሮች ላይ የሚደረገውን ልማት የሚቀንስ ወይም ጨርሶ የሚያስቆም በመሆኑ በተለመደው የድህነት አዙሪት የሚስገባን ወርቅ የሆነ «ምሁራዊ» ትንተና እንደሆነ እነግርዎታልሁ:: ኢትዮጵያችን «ሙቀቱ» ከቁጥጥር ውጭ እንዳይወጣ በጥብቅ እየተከታተለ ልማቱ እንዲቀጥል የሚያደርግ ድፍረት ያለው መንግስት ያስፈልጋታል:: ትክክለኛ ጎዳና ላይ ስለመሆንዋ ከተግባር በላይ የተሻለ ማሳያ ማምጣት አስፈላጊ ባይሆንም የገለልተኛ ባለሙያዎች እማኝነትም አልተነፈጋትም:: የተመስገን ዘውዴ ብሶትም ምንጩ ይኸው:: የኢህአዴግ ፖሊሲዎች አለመክሸፍ::

መንግስት በባንኮች ላይ ያስተላለፍውን አስገዳጅ የ27% ሪዘርቭ ያላስደሰታቸው ተመስገን ዘውዴ የወለድ ምጣኔውን አሁን ባለው መጠን (5%) እንዲወሰን ለምን እንደተደረገ ለማሰብ ፍላጎቱና ጊዜው ያላቸው አይመስሉም:: ጥያቄው ትንሽ ወጠር ቢደረግ ሰዎች በዚሁ ከፍተኛ ግሽበት ወቅት ላይ ተቀማጭ ገንዘባቸውን ከባንኮች ለምን አላሸሹም? ነገሩ የተገላቢጦሽ መሆኑ ግልፅ ነው:: በከፍተኛ ግሽበት ላይ ሆነንም ቢሆን የባንኮች ተቀማጭ ገንዘብ በየዓመቱ 26% በመቶ በላይ የጨመረ መምጣቱን ሪፖርቶች ያስረዳሉ:: ታዲያ ይህ ሁኔታ የአዳም ሲሚዝ ክላሲካል

ኢኮኖሚያዊ ስነ-ሐሳብን ወይንም የ1989ኙ «የዋሽንግተን ኮንሰንሰስን» አይቃረንም? በዚህ ፈታኝ በተባለ ወቅት ኢንቨስተሮች ለምን በሁኔታው ደንብረው አልሸሹም ወይም አዳዲሶቹ ከመምጣት ለምን አልታቀቡም? ወይም እንደ የምስራቅ ኤስያዎቹ ነብሮችና አርጀንቲና አጋጥመዋቸው የነበረውን የፈይናንስ ቀውስ ተከትሎ የመጣውን ጣጣ ለምን በኢትዮጰያ ላይ አልተደገመም? በጥቁር ገበያና በባንኮች መካከል ያለውን የውጭ ምንዛሪው ዋጋ ልዩነት በጣም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? በመጨረሻም የዚሁ ዝቅተኛ የወለድ ምጣኔ ቀጥተኛ ተጠቃሚው ኢንቨስተሩ እንዲሆን መንግስት ሆን ተብሎ ያደረገው እንጂ እሳቸው እንደሚነግሩን መነሻው ድንቁርና አይደለም፡፡ ተመስገን እነዚህንና መሰል ጥያቄዎች ለመመለስ ካልቻሉ መናደድ ያለባቸው በራሳቸው እንጂ ተፈትነው ውጤት ባመጡ የኢህአዴግ ፖሊሲዎች ላይ አይደለም፡፡ ደግነቱ ዓለም ሁሉ የኢትዮጵያን አካሄድ ተረድተዋል፡፡ ተቀብለዋልም፡፡ ወደኋላ የቀሩት ተመስገን ዘወዴና ዕድለ-ቢሱ መድረክ ብቻ ናቸው፡፡

ቋሚ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል እየተጎዳ እንደሆነ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን ከረጅም ጊዜ አንፃር ከድህነት መውጫው ብቸኛ አማራጭ ይኸው ነው፡፡ ኢትዮጰያውያን(ችግሩን በቀጥታ ለሚመለከታቸው) አሁን ያለውን ፈታኝ የኑሮ ሁኔታ ነገ ለልጆቻችን ለምናስረክባት የበለፀገች ሃገር ሲባል በቁርጠኝነት መጋፈጥ ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ስርዓት መፈጠር ምክንያት የሆኑትንና በደምና በህይወት ዋጋ ከከፈሉት ጋር ሲወዳደር ያሁኑ ፈተና በጣሙን የቀለለ እንደሆነ መገንዘብና መቀበል ራሱ ችግሩን የመቋቋም ጉልበት ይሰጣል፡፡ በነዚህ ችግሮች ተሰናክለን ከልማት ሃዲድ ላፍታም ቢሆን እንድንወጣ መፍቀድ የለብንም፡፡ ስለኢኮኖሚው ጉዳይ ባጭሩ ይኸን ያኽል ካልኩኝ ዘንዳ ቀጥየ ፖለቲካውን በሚመለከት ከገብሩ አስራትና መረራ ጉዲና ጋር ላፍታ ያህል አቆያቸዋለሁ፡፡

በኔ እምነት ገበሩ አስራት እንደዛች ዕለት የዘቀጡበት ጊዜ ያለ አይመስለኝም፡፡ለነገሩ በደንብ አስበውበት የተናገሩት መሆኑን ለመቀበል ያዳግተኛል፡፡ በጥያቄ ላጣደፉዋቸው ነውጠኞች ለማባበል ብለው የፈፀሙት የስህተቶች አውራ አድርጌ ወስጀዋለሁ፡፡ ለማንኛውም ለዚህ ስሜት ከዳረጉኝ አባባሎቻቸው እሰኪ ልጥቀስ፡፡ «እኛ በስልጣን እያለን የፈፀምናቸው በርካታ ስህተቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ የኛ አካሄድ ኢትዮጵያን ያለ ባህር አስቀርተዋታል፡፡ ይሄ ደግሞ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገትና መረጋጋት ወይም ሰላም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለው እንገነዘባለን፡፡ ለዚህም እኛም ተጠያቂ እንደሆንን ደጋግመን ተናግረናል፡፡ **ይኸንን የምንለው ግን ወደ ስልጣን ለመመለስ አይደለም፡፡ በዚህ እንዳታስቡ፡፡ እኔ በግሌ ምናልባት ፍትሀዊ የሆነ ስልጣን ዜጎች በመከባበር የሚኖሩባት ሃገር እንደትኖር እፈልጋለሁ፡፡ እንደዚህች ያለች ሀገር እንድትገነባ እፈልጋልሁ፡፡ በግሌ ግን አስተዳዳሪ ወይንም ሚኒስትር ለመሆን ፍላጎት የለኝም፡፡ ታዲያ ለምን ወደ ፖለቲካ ትገባልህ ያላችሁኝ እንደሆነ ግን ከዚህ በፊት ያጠፋሁትን ለመካስ ነው**»

ገብሩ አስራት ስህተት ያሉትን ነገር በምን አማራጭ ሊያስወግዱት (ሊያስቀሩት) ይችሉ እንደነበረ መልስ የላቸውም። ከዚህ በላይ ግን ይህ አቋም በራሱ በዚህ ጊዜ መነሳቱ ለድርጅቱ በምን መልኩ እንደሚጠቅመው አይገባኝም። ኢትዮጵያ የባህር በር የማጣትዋ ጉዳይ እውነት ነው። ገብሩ አስራት ተናገሩት አልተናገሩት ግን ለውጥ አያመጣም። ለምርጫ ይጠቅማል ብለው አስበው ከሆነ ግን ከፍተኛ ስህተት፤ ቀለል ብናደርገው ደግሞ የበዛ የዋህነት ነው። የሚበዛው ኢትዮጵያ ህዝብ የባህር በር ጉዳይ ያበቃለት አድርጎ ይወስዳል። በዚህ የፖለቲካ ክር ተንጠልጥሎ ድምፅ እንደማይሰጥ በተደጋጋሚ ግልፅ አድርገዋል። ሌላውና ዋናውን ጉዳይ ግን ለ30 ዓመታት ደም ያፋሰሰውንና ሃገራችን ካለችበት የድህነት ወለል እንድትገኝ ያደረጋትን ጦርነት ማስወገድ የሚያስችለውን መለኮታዊ ሀይል ከየት እንደሚያመጡ ቢነግሩን ባናምናቸውም ቢያንስ ባልተገረምን ነበር። ስብሰባውን የተካፈሉ ሰዎች ይህንን ለመጠየቅ ፍላጎት አልነበራቸውም ብቻ ሳይሆን ለዘመናት የሰለቸንን የትምክህት አባዜ ደጋግመው በማጨብጨብ ትንሳኤ ሊሰጡት የቀራቸው ነገር አቅም ማጣት ብቻ ነው። ዓለም ያወቃት ኤርትራን ሉዓላዊነት የሚፈታተን ፖለቲካዊ አባዜ መልሶ የሚያደርሰን ከነበርንበት የጦርነት አዙሪት ውስጥ ነው። ይህ ትውልድ እንዲህ ዓይነቱ አዙሪት ዳግም ነፍስ የሚዘራበት ዕድል እንደማይፈቅድ የእስካሁን ተገባራቱ ምስክሮች ናቸው።

ታዲያ ከላይ የገለፅኩት የገብሩ አስራት አመለካከት አይደለም ያስገረመኝ። በ1993 ዓ/ም በህወሓት አመራር በነበረው የፖለቲካ ልዩነት ዋነኛ መከራከሪያ አጀንዳቸው እንደነበረ ስቼውም አይደለም። አዲስ የሆነብኝ ጉዳይ መታገል ለምን እንደመረጡና የአክራሪውን ዲያስፖራ የምሬት ጅራፍ ማሪፊያ እንደሆኑ የሰጡት ምላሽ ነው። የመታገላቸው ሚስጥር «ያለፈውን ሐጥያት» ለመደምሰስ ካለው ጠቀሜታ አንፃር  ይመለከቱላቸው ዘንድ አስቂኝና አሳዛኝ በሆነ መልኩ ገልጸውታል። በኔ  እምነት ግን የከዚህ በፊቱ ሀጥያት ከነበረ የአሁኑ የባሰ ኩነኔ ነው። ከዚሁ አክራሪ ዳያስፖራ የሚገኘውን ፍርፋሪ ለማግኘት ሲባል ወደዚህ ዓይነቱ መጨረሻ-አልባ ውርደት መዝቀጥ ለትግል ሲባል የተከፈለ ዋጋ ስለመሆኑ መቀበል ያዳግተኛል። ገብሩ አስራትና ስየ አብርሃ በተቋዋሚው ጎራ ጥርጣሬ መጠን የትግራይ ህዝብና የሰማዕታቱ ክብርን እስከመንካት የሚደርስ በደል እንደፈፀሙ ይሰማኛል። መድረክ ገብሩንና ስየን «በሰማዕትነት» በማቅረብ የቆሸሸ ፖለቲካውን ለመታደግ ጥረት አድርገዋል። እንደዛም ሆኖ ግን የአክራሪው ዳያስፖራ ልብ መግዛት ስለመቻላቸው የሚያሳይ ምልክት የለም።

በመጨረሻም ከፖለቲከኛነት ይልቅ ወደ ኮሜዲያንነት የሚያደሉት መረራ ጉዲናን እስቲ እንመልከት። እሳቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ መታገልና ታግሎም ለውጥ ማምጣት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል።«ዋና ዓላማችን የኢህአዴግን የከፋፍለህ ግዛ ሴራን ማክሸፍ ነው። የኢህአዴግ ካድሬዎች ትግራይ ሲሄዱ «እኛ ከሌለን» አማራና ኦሮሞ

መጥተው ከቀይ ባህር ውስጥ ይጨምሩዋቸዋል፤ አማራው ጋር ሲሄዱ «እኛ ከሌለን» አሮሞ ኢትዮጵያን ይዞባችሁ ይሄዳል፤ ኦሮሞው ጋር ሲሄዱም መረራና ቡልቻ ነፍጠኛውን አዝለው እየመጡባችሁ ነው እያሉ መሰሪ ዓላማቸውን ያሰርፃሉ፡፡ ባለፉት 3 ዓመታት ትንሽዋን ኢትዮጵያ ጎጆ ፈጥረናል፡፡ ኢህአዴግ ደግሞ ከስልጣን አውርደን ትልቁዋን ኢትዮጵያ እንፈጥራለን» ኢህአዴግ እንዲህ ዓይነቱ የዘቀጠ አስተምህሮ እንደማያስተምርና ነጭ ውሸት እንደሆነ ግልፅ በመሆኑ ከመታዘብ ውጪ የምለው የለኝም፡፡ «ትንሽዋን ኢትዮጵያ ፈጥረናል» ያሉትን ነገር የምራቸው ከሆነ ግን ራሳቸውን ባያታልሉ የሚሻላቸው ይመስለኛል፡፡ መረራ ጉዲና እንዲህ ይበሉ እንጂ ይህ መድረክ የሚባለው ስብስብ አንድ ግንባር እንኳ መፍጠር የተሳነው ነገር ግን ለቁመናውና ለክብሩ አብዝቶ የሚጨነቅ ሀይል ነው፡፡ መድረክ በመሬት፤በፌደራሊዝም፤ በፖለቲካዊ ፓርቲዎች አወቃቀር ላይ የማይግባቡ ሃይሎችን በማሰባሰብ ፖለቲካዊ ስልጣንን ከጨበጠ በኋላ ውሳኔ እንደሚሰጥባቸው ግልፅ አድረጓል፡፡ ከዚህ ሁሉ የባሰው ነገር ግን ለህገመነግስቱና ከዚሁ ለሚመነጫው ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ያለውን ንቀት ክልክ ያለፈ መሆኑ ነው፡፡ መረራ ጉዲና ኢህአዴግን ወደሳቸው ደረጃ ዝቅ ለማደረግ ያደረጉት ጥረትም መነሻው ይኸው የተሳሳተ ግምትና ንቀት ነው፡፡ በዚሁ ስብሰባም በአረቡ ዓለም የተደረጉትን ለውጦች በመሰረቱ በየሀገራቱ ወታደራዊ ሀይሎችና ጀኔራሎች ጥረት የተከናወነ እንደሆነና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስበስብ የሚያደረገውም የፀጥታ ሀይሉ ያለውን ተጨበጭ ሁኔታ ለዚሁ ተግባር የማያመች መሆኑ እንደሆነ በድፍረት ተንትነዋል፡፡ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይል የመረራ ጉዲናን አጀንዳ ሳይሆን ህገመንግስታዊ ተልዕኮ ያለው ሰላማዊውን መንገድ ያልጣመቸው ሀይሎች በመጡበት መንገድ ለማስተናገድ የተዘጋጀ ተቋም እንደሆነ በምን ቋንቋ ማስረዳት ይቻላል?

በተጨማሪም ደፋር እንደሆኑ ለመግለፅ ሲባል ፓርላማ ውስጥ «ኢኮኖሚውን የማታሻሽሉ ከሆነ የኢትየፐያ ህዝብ ተነስቶ ይበላቸዋል» ብለው መናገራቸውን ስለሆነም ከዚህ በላይ «ጀግንነት» ሊገባቸው እንደማይችል ተሰብሳቢዎችን ባስፈነደቀ አኳሀን ለመግለፅ ሞክረዋል፡፡ ደርግን በታማኝ ካድሬነት ላገለገለ ግለሰብ ብልግናና ጀግንነት ቢምታቱበት ማን ይፈርዳል? ቸር እንሁን፡፡